# የኢትዮጵያ መንግስት የኦሮሞ መንግስት አይደለም።

የኦሮሞዎች ለፍትህ፣ ለደህንነት እና ለእውነት (ኦፍደእ)[1]

አቋም

## ዳራ

የኢትዮጵያ መንግስት "የኦሮሞ መንግስት" ነው የሚለው ተረት መንስኤው የአሁኑ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ አሊ በመጋቢት ወር 2010 ወደ ስልጣን መምጣት ነው። ለእርሳቸው ስልጣን መንገዱን የጠረገው በጥቅምት 2008 የተጀመረው አምባገነናዊ አገዛዝን አስወግዶ ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በር የከፈተው የኦሮሞ ፕሮቴስት ተብሎ የሚታወቀው ኦሮሞ ወጣቶች ትግል ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህን ትግል በመፈናጠጥ ወደ ስልጣን ስለ መጡ ምንም እንኳን ጉዳዩ እውነት ባይሆንም "በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ኦሮሞ የአገሪቱ መሪ ወደ ሥልጣን ወጣ" የሚል ትርክትም ተጋኖ መነገር ተጀመረ። በማያያዝም አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር በሀገር ዉስጥም ሆነ በውጭ አገር ሰፊ ድጋፍ ያለው "የለውጥ አራማጅ መሪ" ተብለው ሲወደሱ ነበር።

የኦሮሞ ብሔራዊ ንቅናቄ ግልፅ አጀንዳ ያለው በኦሮሞ ህዝብ መሰረታዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ማኅበራዊ ንቅናቄ ነበር። ይህ ንቅናቄ አንድን ግለሰብ ወደ ስልጣን ለማምጣት ያለመ ትግል አልነበረም። ይልቁንም ኦሮምኛ ተናጋሪ ከመሆኑ ዉጪ ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር የትግል አንደነት ያልነበረውን የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) አባል የሆነ ግለሰብ መሪ አድርጎ ለመሾም የተነሳ የፖለቲካ ንቅናቄ አልነበረም።

የኦሮሞ ብሄራዊ ንቅናቄ በ2008 በኦሮሞ ፕሮቴስት መልክ ሲከሰት መሰረታዊ ጥያቄዎቹ የኦሮሞ ህዝብ እራሱን በራስ የማስተዳደር መብት፣ የመሬት ባለቤትነት እና የማንነት መብቶችን ህገ መንግስታዊ ዋስትና ማስጠበቅ ነበሩ። እነዚህም ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄዎች ጋር የሚጣጣሙ ፍትሃዊ፣ ህጋዊ እና ሥነምግባራዊ መሰረት ያላቸው ጥያቄዎች ነበሩ። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም ነፃ፣ ገለልተኛና ፉክክር ያለበት ምርጫ ተደርጎ ህጋዊ ቅቡልነት ያለው መንግስት እስኪቋቋም ድረስ የቀረውን የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የስልጣን ዘመን የመጨረስ የባለአደራነት ሥልጣን ተሰጣቸው። ይህን ኃላፊነት ይወጣሉ ተብሎ ነበር የተጠበቀውና የታመነው፡

የዐቢይ መንግስት የኦሮሞን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ግብና የተሰጠውን አደራ ወደ ጎን በመተው "ኦሮሞ የመንግስት ሥልጣን ተረክቧል" የሚል ሀሰተኛ ትርክት በመፍጠርና በአንድ በኩል የኦሮሞ ጥያቄ ተመልሷል በማለት በኦሮሞ ህዝብ የሚነሳ ተቃውሞ ለማኮላሸት ሲጠቀምበት፣ በሌላ ወገን ደግሞ ኦሮሞ ካልሆኑ ኢትዮጵያውያን ሊነሳበት የሚችለውን ተቃውሞ ለመከላከል ኦሮሞዎችን "መንግስታችሁ ተነካ" በማለት ለማነሳሳት መሳሪያ ማድረግ ጀመረ።

## ተረኩ: የኦሮሞ መንግስት ተረት አፈጣጠር

ይህ የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ተስፋ የጭቆና ዘመን አልፎ የሕዝቦች መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚሟሉበት ዘመን ጅማሮ በመምሰሉ በህዝብ መሃል የፈንጠዝያ ስሜት ፈጠረ። የሀገር ውስጥ እና የዓለምአቀፍ መገናኛ ብዙሀን አርዕስተ ዜናዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ኦሮሞ ስልጣኑን ተቆጣጠረ የሚለውን ፍጹም የውሸት ትርክት ደጋግመው መዘገቡን ገፉበት። እንደ እውነቱ ከሆነ የነገስታት አገዛዝ በ1966 ካበቃንጥ ጊዜ ጀምሮ ስድስት የኦሮሞ ተወላጆች በፕሬዚዳንትነት ወይም በጠቅላይ ሚኒስትርነት አገልግለዋል። ይሁን እንጂ አውነተኛ ታሪክ በውሸት ተረት ተሸፍኖ "የኦሮሞ መንግሥት" ለሚለው ቅጥፈት ተሰፋፋ ። ይህም በላይ የኦሮሞ ብሄራዊ ንቅናቄን ግቦች ወደ ተራ ፖለቲካ ሹመት ለማውረድ የተነደፈ እኩይ ሴራ ነበር።

ትረካው ወደ ላቀ ደረጃ የተወሰደው ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ታዋቂና እና የተመሰከረላቸው ኦሮሞ ጠል ግለሰቦች ነው። በፀረ ኦሮሞ ንግግሮቻቸው የሚታወቁት መስፍን ወልደማርያም ጠቅላይ ሚኒስትሩን "ወደር የለሽ የማሰብ ችሎታ ያለው መለኮታዊ ስጦታ" በማለት ወደ አምላክነት ደረጃ ከፍ አድርገውት ተደመጡ። ኦሮሞንና ቋንቋውን በመጥላት ዝና ያተረፉት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩን "ኢትዮጵያን ለማክበር ሲሉ ራሳቸውን የሰጡ፤ በሺህ አመታት አንዴ ብቅ ያሉ ድንቅ መሪ" ሲሉ አሞግሰዋቸዋል። ዋና የፖለቲካ ተልእኮውን አዲስ አበባን ከኦሮሞ መከላከል ነው ብሎ የተንቀሳቀሰውና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መርህ አልባ የፖለቲካ ገፀባሕርይ የሆነው ብርሃኑ ነጋ ደግሞ አብይን "ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመ እውነተኛ ኦሮሞ" በማለት ገልጾታል። ታዋቂ ዘፋኞችም አቢይ አህመድን "የሀገር አንድነትን፣ የፍቅርን፣ ዘመን ያወጇ አሻጋሪ

---

[1] አፍደእ ያገሪቱ ሁኔታ ያሳሰባቸው የኦሮሞ ተወላጆች በኢትዮጵያ የመሰረቱት ህቡዕ ድርጅት ነው።

ሙሴ” ብለው በዘፈን አወድሰዋቸዋል። ይህ ሁሉ ውዳሴ የታጀበው ደግሞ የሀገሪቱን "ታንኮች እና ባንኮች" ኦሮሞ በቁጥጥሩ ስር አዋለ የሚለውን ጉዳይ በመደጋገም ኦሮሞ ያገሪቱን መከላከያና ሀብት የግል ውርሱ አደረገ የሚል ዓይን ያወጣ ውሸት በህዝብ ውስጥ ለማስረጽ ባለመ የሚዲያ ዘመቻ ነበር።

ለዐቢይ አህመድ ያደሩ የኦሮሞ አክቲቪስቶች እና ፖለቲከኞች የኦሮሞ ጠሎችን ቅስቀሳ ተረክበው ኦሮሞን ከኢትዮጵያ ኢምፓየር ስር ከቆየው የመቶ አመት ግፍ እና ስቃይ ኦሮሞን ነፃ የሚያወጣ ሰው ነው እያሉ ዐቢይን መሲሃዊ ልዑክ አድርገው ገፅታውን መገንባት ጀመሩ። ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል አንዳንዶቹ የኦሮሞ ትግል አንጋፋ መሪዎች የነበሩ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ከስደት ኑሮአቸው ሥራ ፍለጋ ወደ ሀገር ቤት የተመለሱ ጀሌዎች ናቸው። ሁለቱም ቡድኖች የአብይ ጠቅላይ ሚንስትርነት ከኦሮሞ ነፃነት ጋር አንድና አንድ መሆኑን የኦሮሞን ህዝብ ማሳመንን ተልኮአቸው አደረጉ። የአገሪቱን የተሳሳተ አካሄድ ያስተዋሉ እና በዚያ ጎዳና መቀጠል እንደማይገባ ያስጠነቀቋቸውን ተቺዎች የአብይን “የማደናገርና የማሳመን” ፖለቲካ ስልት መረዳት የተሳናቸው ሞኞች በማለት ዘለፏዋቸው፣ እርባና የሌላቸው ምላሰኞችና ቅናት የተጠናወታቸው ምቀኞች ብለው ፈረጁአቸው።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ "የኦሮሞ መንግስት" ተረት ዓላማው የአማራ ፋኖ ኦሮሞን እንደ ህዝብ ለማጥፋት የተነሳ አደጋ ነው በማለት ዐቢይ አህመድን መካች አድርገው በማቅረብ ህዝብን ማደናገር ነው። ይህንን ሲሉ ግን ፋኖ በዐብይ ይሁንታና ድጋፍ ዘንባባ ተሰጥቶት የትግራይ እና የኦሮሞ ብሄርተኝነትን ለመዋጋት እና የ"ጎሳ" ፌደራሊዝም ትሩፋትን ለመታገል የተደራጀ ፣ የሰለጠነ እና እስከ ጥርሱ ድረስ የታጠቀ መሆኑ አይታያቸውም። እውነታውም ይህ ታጣቂ ሃይል ዐቢይ የፈጠረው የፖለቲካ ችግር ውጤት ነው። አሁን የዐብይ ተላላኪዎች የኦሮሞን ህዝብ ከ"ኦሮሞ መንግስት" ጎን እንዲቆምና የገዛ ራሱ ፍጡር የሆነውን ፋኖ “የዓለም መጨረሻ” እንዳያመጣ እንዲታገሉ ሲማጸኑ ማየት አጅግ የሚያስገርመውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ቢሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህን “የኦሮሞ መንግስት” ተረት የሚያጠናክር ብዙ ጠብ ጫሪ ዲስኩሮች አሰምቶአል። በጥቅምት ወር 2011 የሱን የለውጥ ጉዞ የተቃወሙ ወታደሮች እንደተዘገበው “መንግስትን ለመጣል” ወደ ቤተ መንግስት ሄደው ነበር። ዐቢይ በዕለቱ ስለሆነው ጉዳይ ለፓርላማ ሲገልፅ ፣ በመዲናዋ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሞ ወጣቶች “መንግስታችን ተነካ” በማለት ወታደሮቹን ለመጋፈጥ ወደ ዋና ከተማዋ ጉዞ ጀምረው እንደነበር አውርቷል ።ይህ ሽፍጠኛና አነሳሳሽ ንግግር አብይ ተቃዋሚዎቹ የሚገዳደሩት በፖለቲካ ሳይሆን በኦሮሞ ማንነቱ ምክንያት መሆኑን ከገለጸባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አንዱ ነው።

**ክንውኑ: ተቃውሞን ማጥፋት፣ ኦሮሚያን መቆጣጠር**

መጋቢት 24፤ 2010 ዐቢይ አህመድ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን ሲረከብ፤ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመክፈቻ ንግግሩ ለሽግግር ወቅት አቅጣጫ ጠቋሚ፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እና ለዴሞክራሲ ትግበራ ጅማሮ የሚያገለግል ፍኖተ ካርታ ያቀርባል ተብሎ ተጠብቆ ነበር። በትግላቸውና ብዙዎችን ሰውተው ለስልጣን መንገዱን የከፈቱለትን የኦሮሞ የተቃውሞ ንቅናቄ ወገኖች ጥያቄዎችም በተሳካ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር እንደሚፈታ ታምኖ ነበር። ይሁን እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ንግግሩ ወደ ሁዋላ ተመልካች፤ ያለፉትን ሥርአቶች ናፋቂ፤ ያልነበረን የኢትዮጵያን ገናናነት የማስመለስ ትርክት ማቅረብን መርጦ ተከሰተ። ዘግይቶ በብዛት የታየው በብሄሮች የነጻነት ትግሎች ላይ ያነጣጠሩ የንቀትና የማጣጣል ንግግሮች ጅማሮም በዚሁ ንግግሩ ውስጥ ተስተውሏል። ንግግሩ የፍቅር፣ የፍትህ እና የሰላም ሰበካ የተሞላበት ቢመስልም፤ በአጠቃላይ ሲታይ የማይቀር ግጭት መክፈቻ ነበር። ገና ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ከመግባቱ ዐቢይ ለቀድሞ ጨቋኝና ጨካኝ ነገሥታትና ከጥቂት አሥርተ ዓመታት በፊት ለነበረው ወታደራዊ አምባገነን መሪ እንኳዋ ሳይቀር ያለውን አድናቆት በተመረጡ ቃላት በማዥጎድጎድ ምስጋና ሲያቀርብ ተሰማ፡፡

የለውጡ አቅጣጫ ችግር ያለበት ቢሆንም ዐብይ አህመድ ግን ኢትዮጵያን ወደ “ታላቅነቷ” የመመለስ አላማን የማሳካት ሕልም አለኝ ማለቱን ተያያዘው። ጠቅላይ ሚንስትር ሆኖ ከተሾመ ብዙም ሳይቆይ በአንድ የኦህዴድ አመራር ስብሰባ ላይ ባደረገው ንግግር ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በስልጣን ላይ ለሰላሳ አመታት መቆየት የቻለው በትግራይ ክልል አንዳች ተቃውሞ እንዳይነሳ በማዳፈን እንደሆነ አስረዳ። ኦህዴድም በተመሳሳይ ስልት በኦሮሚያ የሚነሱትን ማንኛውንም ተቃውሞ ባለመታገስ ክልሉን ከተቃውሞ የፀዳ ማድረግ የፓርቲያቸው ብቸኛ የፖለቲካ መሰረት መሆን እንዳለበት አሳስቦአል። በዚሁ ዕሳቤ የኦህዴድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀገርን በህገ መንግስቱ ከማስተዳደር እና አስፈላጊ መንግስታዊ ግልጋሎቶችን ለሕዝብ ከመስጠት ይልቅ ስልጣንን መጠበቅ እና ማስጠበቅ ተቀዳሚ ተልእኮው አደረገ። ለዚህም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ተቃውሞ ጸጥ ለማሰኘት፣ ለማሽማቀቅ እና ለማስወገድ ለከት የሌለው ሽብር እንደ መሳሪያ ተመርጦ ወደ ተግባር ተገባ።

ዐብይ የመጀመሪያው ሰለባው ያደረገው የታገለለት ዓላማ በመካዱ ምክንያት በቁጭት ተነሳስቶ የነበረውን የኦሮሞ ወጣት ነው። ወደ ሥልጣን ያመጣውን የኦሮሞን ተቃውሞ የሚመስል የወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዳግም እንዳይከሰት በእንጭጩ ለመቅጨት ወሰነ። በዚህም መሰረት አገዛዙ በአዳማ የኦሮሚያ ወጣቶች ተወካዮችን ለውጡ የደረሰበትን ደረጃ

ለማሳወቅ በሚል ሰበብ ለስብሰባ ጠራ። በስብሰባው ላይ ለተገኙ ወጣቶች የተሰጠው ምርጫ ወይ ወደ ኦህዴድ እንዲቀላቀሉ እና የፖለቲካ መስመሩን እንዲከተሉ፤ አለያም ከፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ራሳቸውን እንዲያገሉ ነበር። ከዚያ በኋላ ወደ ገዢው ፓርቲ አባልነት ለመቀላቀል ፈቃደኛ ያልሆኑትን የኦሮሞ ወጣቶችን ማዋከብ፣ ማሰር፣ መግደልና አስከሬናቸውን አውሬ እንዲበላው በየስርቻው መጣል የዐቢይ አገዛዝ ቀዳሚ ተግባር ሆነ። በግንቦት 6 ቀን 2012 የተገደለው የምስራቅ ሀረርጌው መሐመድ አሚን በዚህ መልኩ ከተገደሉት በሺዎች ከሚቆጠሩት ወጣቶች አንዱ ነው። በኦሮሞ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ጊዜ የምእራብ ሸዋ ዞን አስተባባሪ የነበረው ገላና ኢማና ህዳር 11 ቀን 2013 አምቦ ላይ ተይዞ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎ በሚስጥር በማይታወቅ ቦታ ተቀበረ። በዚያው ሳምንት በኦሮሚያ የተለያዩ ከተሞች በርካታ የኦሮሞ ተቃውሞ መሪዎች ተይዘው ተገድለው፣ አስከሬናቸው በወንዝ ዳርና በመንገድ ዳር ተጣለ። በዚህ መልኩ ከእስር ቤት እያወጣ በመግደልና በጭካኔ ግድያ ዛቻ አማካይነት ለጊዜውም ገናናውን የኦሮሞ ወጣቶች እንቅስቃሴ ለማምከንና ለማቀዝቀዝ ቻለ፡፡

የዐቢይ አገዛዝ ይህንን እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ በጅምላ እስር እና ንብረት መውረስን ጨምሮ ሰላማዊ ዜጎችን ለማሸበርና ለማንበርከክ ይጠቅማል ያላቸውን ሌሎች እርምጃዎችንም ወስዷል ። አንድ ተደማጭነት ያለው ታዛቢ እንደሚለው፣ ኦሮሞ በቅርብ ግዜ ታሪኩ ከዚህ የባሰ ጨካኝ ሁኔታ አላየም። በእርሱ አገላለጽ *የኦሮሞ ማህበረሰብ በጦርነት እና በስደት ዳሽቋል። ዛሬ ሸገር እየተባለ በሚጠራው ከተማ በየቀኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተሰብስበው የሚታጎሩበት 30 እስር ቤቶች አሉ። ከ100,000 ያላነሱ የኦሮሞ የፖለቲካ እስረኞች በኦሮሚያ አሉ። ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ነገር አልተከሰተም። ይህን ያህል የፖለቲካ እስረኛ ያለው ሌላ ክልል የለም። በኦሮሚያ በየቀኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ይገደላሉ። በሸዋ፣ በወለጋ፣ በጉጂ እና በአርሲ ያሉ የኦሮሞ ገበሬዎች እንደዛሬው ገሃነም የሚመስል ሁኔታ ውስጥ ፍጹም ኖረው አያውቁም። የቤተሰቡ አባወራ ታፍኖ ይወሰዳል፤ አንዱ መጥቶ በሬዎቹን ይዘርፋል። ተመልሶ ሲመጣ የአገዛዙ ታጣቂዎች ደግሞ የቀሩትን እንስሳት ከዓመፀኞች ጋር ተባብረሃል በሚል ክስ ይወርሱበታል። በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ህዝቡ የፖለቲካ መጫወቻ ሆኖአል። ባለፉት አምስት ዓመታት የተገደሉት ሰዎች ቁጥር በኃይለሥላሴ፣ በመንግስቱ እና በመለስ ዘመን ከተገደሉት ጠቅላላ ቁጥር በእጥፍ ይበልጣል።.*

ዛሬ የዐብይ አገዛዝ የኦሮሞን ህዝብ በማስፈራራት ታዛዥና ጥያቄ የማያነሳ ዜጋ ለማድረግ ያስችለኛል ያለውን የታሰበበት ሽብርና ግድያ ወደ መፈጸም ተሰማርቷል። የጸጥታ ሃይሎች በመላው ኦሮሚያ በወጣት ሴቶችና ወንዶች ላይ ግድያ በየዕለቱ ይፈፅማሉ። ወላጆች ያለ ጧሪ ቀባሪ፣ሕፃናት ያለ ወላጅ ቀርተዋል፡፡ በጥቅምት ወር 2023 ማገባደጃ ላይ የሰባት ልጆች እናቷ የምስራቅ ሸዋ ቦሰት ነዋሪ የነበረችው ኩሊ ሀዋስ ከሌሎች ሁለት እናቶችና ጋር በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድላለች። የርሷ ዓይነት ዕጣ ፈንታ ከደረሳቸው በሺዎች የሚቆጠሩ እናቶች ጋር ተቆጠረች። በርሷ ላይ የተፈፀመው ጭካኔ እና ኢሰብአዊ ድርጊት አጅግ ዘግናኝ በመሆኑ በስፋት እንዲሰማ ሆነ እንጂ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገደሉ እናቶች በሺዎች የሚቆጠሩ ናቸው። ግንቦት 3 ቀን 2013 በምዕራብ ኦሮሚያ በደምቢ ዶሎ አማኑኤል ወንድሙ በፀጥታ ኃይሎች በአደባባይ የተገደለው እናቱ ቆማ እንድትመለከት ተደርጎ ነው። አስከሬኑን ለመጠየቅ እና ለመቅበር ለሰዓታት ተከልክላለች። ታሪካቸው ሚዲያ ላይ አልወጣም እንጂ በመላው ኦሮሚያ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ እንደ አማኑኤል እናት ያሉ ወላዶች ልጆቻቸውን፣ባሎቻቸውን እና ኑሯቸውን አጥተዋል፣።

የኦሮሞን ተቃውሞ ሲመሩ የነበሩ አርቲስቶች እና አክቲቪስቶችም ከዚህ ግፍና እንግልት እንዲሁም ግድያ አልተረፉም። ሰኔ 22 ቀን 2012 ታዋቂውና ተወዳጁ የኦሮሞ አርቲስትና አክቲቪስት ሀጫሉ ሁንዴሳ በአዲስ አባባ ተገደለ።፡በማግስቱ መንግስት የአስከሬን ምርመራ ሳያደረግ የሟቹን አስከሬን ለመቅበር ተቻኮለ። ይህ ደርጊት በወቅቱ የነበረውን የገዳዩን ማንነት የመሸፋፈን ሙከራን አመላካች ነበር። ነገር ግን ቀድመው የተፈጸሙ በርካታ ሚስጥራዊ ግድያዎችን ለታዘበ የግድያው ፈጻሚ ማን እንደሆነ ግልጽ ነበር። በቀጣዮቹ ቀናት የግድያው አረመኔያዊነት እና የአርቲስቱን የቀብር ስነስርዓት ለማስፈጸም የተነሱት ባለስልጣናት አካሄድ በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሳ። አርቲስቱ ከመቀበሩ በፊትም የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች የሆኑት ከኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) በቀለ ገርባ፣ ጃዋር መሀመድ እና ደጀኔ ጣፋ፣ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ኮሎኔል ገመቹ አያና፤ ሚካኤል ቦሩ፤ ለሚ ቤኛ እና ኬነሳ አያናን ጨምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ታሰሩ። በዚህ ወቀት የፀጥታ ሀይላት በወሰዱት እርምጃ በኦሮሚያ 10ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ታስረዋል፤ በትንሹ 177 ሰዎች ተገድለዋል፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ቆስለዋል።

ቀጣዩ የዐቢይ አህመድ አገዛዝ ኢላማ ያደረገው በከተሞች የሚፈፀመውን ግፍ ሸሽተው ወደ ገጠር ገብተው ታጣቂዎችን የተቀላቀሉት የኦሮሞ ወጣቶች ላይ ነበር። አገዛዙ በታጣቂዎችና በኦሮሞ ህዝብ ላይ ሊጠቀምበት ያሰበውን የጥፋት ስልቱን ደብቆ አያውቅም። የካቲት 20፣ 2013 በኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲ የቢሮ ሃላፊ የሆነው ፍቃዱ ተሰማ ለኦሮሚያ ጨፌ ባደረገው ንግግር እንዲህ አለ፡- “*የታጠቁ አማጽያን ጋር የሚደረግ ውግያ ከተለምዷዊ ጦርነት የተለየ ነው። አማፂዎቹ የሚኖሩትና የሚደገፉት በሚንቀሳቀሱበት አካባቢ በሚኖረው ህዝብ ነው። … ስለሆነም እነሱን የማስወገድ መንገድ ከዓሣ ማጥመድ ጋር ተመሳሳይ ነው። በአትላንቲክ ወይም በፓሲፊክ ውቅያኖስ ውስጥ ያሉትን ዓሦዎች በማጥመድ ለቅሞ መጨረስ አይቻልም። ማጥፋት የሚቻለው ውቅያኖሱን በማድረቅ ነው።*”

ይህን “ውቅያኖሱን የማድረቅ” ተልዕኮ ለመፈጸም ወታደሮች እና ጸጥታ አካላት ተመድበዋል። የዐቢይ አህመድ “የለውጥ አራማጆች” መንግስት ስልጣን ይዞ ስድስት ወራት ሳይሞላ ከውጭ ተመልሰው ወደ ፖለቲካው መድረክ በገቡት የኦነግ

ተዋጊዎች ላይ በህግ ማስከበርና የፀረ-ሽምቅ ዘመቻ ስም ጦርነት ተከፈተባቸው። በመቀጠልም አገዛዙ በደቡብ ኦሮሚያ በጉጂ ዞን እና በምዕራብ ኦሮሚያ አራቱ የወለጋ ዞኖች ላይ ኮማንድ ፖስት ወይም ወታደራዊ አስተዳደር በማቋቋም በሰላማዊ ዜጎች ላይ ማንገላታት፤ ግድያ እና አውዳሚ ወንጀል መፈጸም ጀመረ። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት (ኦነሠ) ቤተሰብ አባላት ላይ የተፈጸሙ አሳዛኝ ግፎች መታየት የጀመሩት በዚህ ወቅት ነበር። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ደጋፊዎች ናቸው የተባሉትን ቤቶቻቸውን ማቃጠል፣ አርሶ አደሮች የደረሱ ሰብሎችን እንዳይሰበስቡ መከልከል፣ የከተማ ነዋሪዎች ወደ ገጠር እንዳይሄዱ ማገድ የዚህ እኩይ ተግባር አካል ሆነ። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደ እስር ቤት ተጋዙ፣ በጊዜያዊ ማጎሪያ ካምፖች እና በግል እስር ቤቶች ውስጥ እንዲሰቃዩም ተደረገ፣ ለኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ርኅራኄ አላቸው የተባሉ ሁሉ የዚህ ዘመቻ ሰለባ ሆኑ። ከቤተሰብ አባል የሆነ ሰው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊትን በመቀላቀሉ ብቻ ወላጆች ወንድሞች እና እህቶች ተገደሉ ወይም ታሰሩ፤ ቤታቸው በእሳት ተቃጠለ።

የፀረ-ሽምቅ ውግያ ዘመቻ በ2011 መገባደጃ ላይ ከተጀመረ ወዲህ የኦሮሚያ ክልል በአሰቃቂ ጦርነት ውስጥ ይገኛል። በጥር ወር 2012 በተደረገው የመጀመሪያ ዙር ዘመቻ እስከ ስምንት የሚደርሱ የኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ክፍል ጦሮች፣ በተጨማሪም የፌደራል ፖሊስ፤ የፌደራል ፈጥኖ ደራሽ ሃይል፣ የኦሮሚያ ልዩ ሃይል፣ የኦሮሚያ ፖሊስ፣ የአማራ ልዩ ሃይል እና የአማራ ፋኖ እንዲሁም ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት አመሳስሎ መንግስት ያሰለፋቸው ታጣቂዎች በክልሉ ልዩ ልዩ ቦታዎች በተለይም በወለጋ በአራቱ ዞኖች ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ እና በተለያዩ የጉጂ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ የኦሮሞን ህዝብ “ውቅያኖስ ለማድረቅ” ሲሉ በሰየሙት ስልት በጅምላ ሲጨፈጭፉ ቆይተዋል ።

ይህ የግድያና የጭፍጨፋ ተግባር በብዛት ለመግደል ያመቸው ዘንድ በዘመናዊው የጦርነት ቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ተደርጎአል። ከጥቅምት 9፣ 2015 እስከ ህዳር 17፣ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ በሰው አልባ አውሮፕላኖች እና በአየር ሃይሉ የቦምብ ድብደባዎች በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጭፍጨፋ ተፈጽሟል፣ በዚህ ድብደባም በድምሩ 443 ንጹሃን ተገድለዋል፤ 277 ቆስለዋል። ጥቃቱ ከደረሰባቸው ቦታዎች መካከል የሚከለተሉት ይጠቀሳሉ:: ምእራብ ሸዋ ዞን፤ ሜታ ወልቂጤ ወረዳ፤ ጎሮ ቁሩፔ መንደር፤ (ጥቅምት 9፣)፣ምዕራብ ሸዋ ዞን፤ ጮቢ ወረዳ፣ በከር ኦፉ መንደር፣ (ጥቅምት 12 እና 13); በምስራቅ ወለጋ፤ የኑኑ ቁምባ ወረዳ (ጥቅምት 12); በምስራቅ ወለጋ ዞን፤ ዋዩ ቱቃ ወረዳ ቦናያ ከተማ(ጥቅምት 17); ምስራቅ ወለጋ ዞን፤ በዋማ ሀጋሎ ወረዳ፣ የቀሶ መንደር (ጥቅምት 18)፤ ምስራቅ ወለጋ፡ ዋዩ ቱቃ እና ዋማ ሃገሎ ወረዳዎች፣ (ጥቅምት 23); መራብ ወለጋ ዞን፡ ቂልጠካራ (ጥቅምት 22); ምዕራብ ወለጋ ዞን፤ ቦጂ ቢርማጂ ወረዳ፣ ቢላ (ጥቅምት 23); ምዕራብ ወለጋ ዞን፤ ማና ሲቡ ወረዳ፣ መንዲ (ጥቅምት 30); ምዕራብ ሸዋ ዞን፡ጮቢ ወረዳ፡ ዶቅዶቄ (ህዳር 5); ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ደራ፤ ራቾ በረሳ፣ (ህዳር 6) ምዕራብ ሸዋ ዞን አምቦ ወረዳ፣ዋዴሳ(ህዳር 7)፤ ምዕራብ ወለጋ ዞን፤ ቤጊ ወረዳ፤ ሎፒ መንደር (ህዳር 11); ሆሮ ጉዱሩ ዞን፤ የፊንጫ መንደር (ህዳር 17).

በሮይተርስ ጋዜጠኛ የቀረበው በመረጃ የተደገፈ የምርመራ ዘገባ እንደሚያመለክተው የኦሮሚያ መንግስት በኦሮሚያ ከፍተኛ የመንግስት እና በክልሉ የገዥው ፓርቲ ባለስልጣናት የሚመራ የደህንነት ኮሚቴ (Koree Nageenyaa) የሚባል የግድያ ቡድን አቋቁሞአል። ኮሚቴው በ2012 የተቋቋመው በጊዜው የወጣቶች ተቃውሞ እንዳይበረታና የኦህዴድ አገዛዝን እንዳይቃወም ለመከላከል ነበር። ይህ ገዳይ ኮሚቴ በኦሮሚያ ክልል በ19 ዋና ዋና ከተሞች እና 21 ዞኖች ተቋቁሞ የሃጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ የተነሳውን ተቋውሞ ለማክሸፍ ወደ ተግባር ገብቷል። የኮሚቴው ዋና አመራሮች፣ የኦሮሚያ ፕሬዝደንት እና የክልሉ የብልጽግና ፓርቲ ቢሮ ኃላፊ ሲሆኑ በድምፃዊው ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ወቅት የጸጥታ ሀይሎች እያንዳንዱን ተቃዋሚ በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ ካልተቻለ ደግሞ በጥይት እንዲገድሉ ትእዛዝ አስተላልፈዋል። ይህን ተከትሎም ቢያንስ 200 ሰላማዊ ሰዎች ተገድለዋል፣10,000 የሚሆኑት ደግሞ ታስረዋል።

በቀጣይነት የተደረጉ ድርጊቶች እንደሚያሳዩት የደህንነት ኮሚቴው በኦሮሚያ ውስጥ የሚፈጠሩትን የተቃውሞ ምልክቶች አስቀድሞ ለመቆጣጠር የተጠረጠሩትን ተቃዋሚዎች በመግደልና በመሰወር ሥራ ላይ የተሰማራ የሚስጥር ድርጅት መሆኑን ነው። ኮሚቴው ከህግና ከፍርድ ቤቶች እይታ ውጭ የሚንቀሳቀስ ሲሆን እንደአጋጣሚ በዚህ ኮሚቴ የተያዘ ሰው በፍርድ ቤት ህግ ፊት ቢቀርብ እንኳን ከኮሚቴው አስፈሪነት የተነሳ ዳኞች እና አቃብያነ ሕግ ጉዳዩን ማየት ሲፈሩ ይታያል። ምክንያቱም ዳኞች፤ አቃብያነ ሕግ እና ጠበቆች ሳይቀር በዚህ የግድያ ቡድን ማስፈራሪያ፣ድብደባ፣እገታና ግድያ ሲደርስባቸው እንደነበረ ስለሚታወቅ ነው ::

በኦሮሚያ ክልል አመራሮች በቀጥታ ከታዘዙት ግድያዎች መካከል አንዱ በህዳር 22 ቀን 2014 በ14 የከረዩ ገዳ ምክር ቤት አባላት (አባ ገዳዎች) ላይ የተፈፀመው ነው። *የደህንነት ኮሚቴው ውሳኔ አስፈፃሚዎች* ለገዳዮቹ የሰጡት ትዕዛዝ “ማንንም አታስቀር። ሁሉንም ረሽን” የሚል እንደነበር ተዘግቧል። ይህ ስለ ጭካኔያቸው ማሳያ ከመሆኑም በላይ ሁኔታው አስደንጋጭም ነው። ይህ የተደረገው የገዳ ምክር ቤት አባላትን ለመቅጣት ብቻ አልነበረም። ይልቁንም የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊት (ኦነሰ) አደረገ ብለው በማሳበብ “ውቅያኖስን ለማድረቅ" በሚለው ስልታቸው ህዝቡ ላይ ዘመቻ ለመጀመርና የኦሮም ነጻነት ሰራዊት ድጋፍ እንዲያጣ ማድረግ ነው። ይህ ግድያ በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ የወንጀለኝነት ባህሪይ የሚያሳይ ነው። ይህ መንግስት የትኛውንም ብሄር የማይወክል ወንጀለኛ መንግስት ስለሆነ “የኦሮሞ መንግስት” ሊባል አይችልም።

**ቅልበሳው: አንድ እርምጃ ወደፊት፣ ሶስት እርምጃ ወደ ኋላ**

በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ከአፍሪካ ህብረት ታዛቢ ቡድን በስተቀር አለም ሁሉ ነፃ እና ኢፍትሃዊ አይደለም በማለት ውድቅ የተደረገውን ምርጫ "በማሸነፍ" ስልጣን የያዘ የወንጀለኞች ስብስብ ነው። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያን እየመራ ያለው ሀገርን የከዳ ቅጥረኛ መንግስት ነው። የሀገሪቱ ሉዓላዊነት እንዲደፈር ከማድረግም አልፎ የውጭ ኃይሎችን ጋብዞ በአገሪቱ ዜጎች ላይ አሰቃቂ ወንጀል እንዲፈጽሙ ያደረገ ነው። ሐገሪቱ ዛሬ እየተመራች ያለችው የጦር ወንጀሎችን፣ በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን፣ የዘር ማፅዳት እና ምናልባትም የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን በፈጸሙ አካላት ነው። ይህ አገዛዝ የሰብአዊ መብት ጥሰትን በማናለብኝነት የፈፀመ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ታጣቂዎችን በመፍጠር በንጹሐን ላይ ዘግናኝ ጥቃት እንዲፈጽሙ ያደረገ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ላሉ ችግሮች በውይይት የፖለቲካ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ፖለቲካውን በጦረኝነት የቀየረ በዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የተወገዘ ቡድን ነው።

የዚህ መንግስት የወንጀል ተግባራት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽንን ጨምሮ በገለልተኛ እና ታማኝ አለም አቀፍ ድርጅቶች የተመዘገበ ነው። በሥልጣን ላይ ያለው ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን ከያዘ ሶስት አመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው ዘገባ የጅምላ እስራትን፣ ያለ ክስ ለረዥም ጊዜ ማሰርንና፣ የዜጎችን መብት የሚጥሱ ህገወጥ ፍተሻዎች ማድረግ የዕለት ተግባሩ እንደሆነ አጋልጧል። የመሰብሰብ፣ የመናገር እና በነፃ የመንቀሳቀስ ገደብ፣ የአካል ድብደባ፣ ማሰቃየት፤ አልፎ ተርፎም ከህግ አግባብ ውጪ የሚፈጸሙ የበቀል ግድያዎችን ከዚህ ቀደም ከነበረው በከፋ መልኩ መቀጠሉን አረጋግጦአል። አንዳንዶች ይሄንን መንግስት እንደ ኦሮሞ መንግስት ለማቅረብ በትጋት ቢጥሩም፤ ኦሮሚያ ግን መንግስት በህዝቡና በተቋዋሚዎቹ ላይ በሚወስደው ጭካኔ የተሞላበት ግድያዎች፣ በህገ ወጥነት እና በግድየለሽነት በሚፍፅማቸው ተግባራት ከቀን ወደ ቀን መመለሻ ወደሌለው ገደል ውስጥ እየገባች ነው። (አምነስቲ ኢንተርናሽናል, *ከህግ ማስከበር ባለፈ፡ በኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች በአማራ እና ኦሮሚያ የሰብአዊ መብት ረገጣ,* 2020 ይመልከቱ)።

ሌላው ቀርቶ በመንግስት የተቋቋመውና በደካማነቱ የሚተቸው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከህግ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ የዘፈቀደ እስራት፣ ማሰቃየት፣ መሰወር፣ የህዝብ ንብረት ምዝበራ እና ሌሎች የመብት ጥሰቶችን በመረጃ አስደግፎ ሪፖርቶችን በተለያዩ ወቅቶች አውጥቷል። የካቲት 16 ቀን 2016 ያወጣው የመጨረሻው ሪፖርት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተለይም ህገ-ወጥ ግድያዎች በሚያስደነግጥ መልኩ እየጨመረ መምጣቱን ገልፆአል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት በምስራቅ ጉጂ አዳዲ በሚባል መንደር የሞባይል ስልኩ በህዝብ ስብሰባ መሃል በድንገት በመጮሁ ጀርባው ላይ በጥይት ተመትቶ በግፍ ከተገደለው አሪቲ ሹኑንዴ አንስቶ እስከ ካረፈበት ሆቴል ተወስዶ በጥይት ተደብድቦ ሬሳው መንገድ ላይ የተጣለው የኦነግ አመራር በቴ ኡርጌሳ ድረስ ያለውን ህገወጥ የጭካኔና የግፍ እርምጃዎች በበርካታ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ደረጅቶች ርፖርቶች ላይ ሰፍረው እናገኛለን።

**ማጠቃለያ**

ያለፉት ስድስት ዓመታት ያረጋገጡት ብቸኛ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያው መንግስት ለለውጥ የማይመች ስለመሆኑ ለረጅም ጊዜ የነበረንን ጥርጣሬ ነው። ብዙ ነገሮች የተለወጡ በመሰሉ መጠን ምንም ነገር እንዳልተለወጠ እንታዘባለን። ለውጥ መጣ ቢባልም ሀገሪቱን ወደ ከፋ ሁኔታ ከመሄድ አያቆማትም። አሁን ኢህአዴግን በመተካት ስልጣን የተያዘው እጃቸው በደም በተጨማለቀ የመዝባሪዎቸ ስብስብና (kleptocrats) በሁሉም መመዘኛ ውራ በሆኑ ነሆላሎች በሚመራ (kakistocracy) አምባገነናዊ አገዛዝ ነው። ይህ የኛ ድምዳሜ ብቻ አይደለም። መንግስትን በዋና ቃል አቀባይነት ሲያገለግል የቆየው አቶ ታዬ ደንደአም የዐብይ መንግስት "የኦሮሞ መንግስት ነው" የሚለውን ትርክት ሲያራግብ ከርሞ በዚህ መንገድ ለመቀጠል ኀሊናው መሸከም ሲያቅተው በአደባባይ የሰጠው የምስክርነት ቃል ነው። ታዬ የሥራ ስንብት መልዕክቱን በዚህ መልክ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቧል፡- *"የተናገሩትንና የጻፉትን የመደመር እሳቤ አምኜ ተከተልኩዎት። አሁን ግን በተናገሩት የማይኖሩ ብቻ ሳይሆኑ በሰው ደም የሚጫወቱ አረመኔ መሆንዎን ተረድቼአለሁ። እውነት መስሎኝ በሀገር ህልውና ስም ሲያካሂዱ የነበረውን ኢትዮጵያዊያንን ከማገዳደል አልፎ ሀገሪቱን ያደቀቃትን ከንቱ ጦርነት ሳዳምቅልዎ በነበረበት ወቅት ሲያወድሱኝ ነበር። ዛሬ ነገሩ ገብቶኝ የወንድማማቾች መገዳደል ይቆም ዘንድ ለሰላም በመወገኔ ከሰልጣን አነሱኝ። ለወንበርና ለመኪና በመገዛት ኦሮሞን በኦሮሞ ለማጥፋትና ኦሮሞን ከወንድሞቹ ጋር ለማጣላት የሚጫወቱትን ቁማር እያየሁ ዝም ባለማለቴ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ሰለነበረን አጭር ቆይታ አመሰግናለሁ። እስካለሁ ድረስ ለሰላምና ለህዝቦች ወንድማማችነት የማደርገው ትግል ይቀጥላል."*

*ፊንፊኔ*

*ሚያዝያ* 22 2016